# የእውቀት መብዛት

*"… ዳንኤል ሆይ፥ ……… እውቀትም ይበዛል"! (ዳን.12:4)*



የመጨረሻው ዘመን ትውልድ የሚታወቀውም በእውቀት ነው። የስነሰው ጥናት እንደሚያመለክተውም የሰው እውቀት በየስምንት አመቱ እጥፍ እየሆነ መጥቷል። ከቀደመው ዘመን ይልቅ **80%** ታላላቅ ሳይንቲስቶችና ተመራማሪዎች የሚኖሩት በዚህ ዘመን ነው። በየ**ደቂቃው** እነዚህ ምኁራን በሰው እውቀት ላይ 2000 ገጽ በሰው ሳይንሳዊ እውቀት ላይ ይጨምራሉ። በየ24 ሰዓቱ የሚጽፏቸውና የሚበረክቷቸው ሳይንሳዊ ግኝቶች ለአንድ ሰው ለማንበብ 5 አመት ይፈጅበታል። ከግማሽ ሚሊዮን በላይ መጽሐፍትም በየአመቱ ይታተማሉ።

አፖሎ(Apollo)13 የተባለችው የጠፈር መንኮራኩር ስትጠፋ ኮምፒውተር ፈልጎ ሊያገኛት የቻለው በአንድ ሰዓት ተኩል ጊዜ ውስጥ ነበር። ኮምፒውተር ባይኖር ኖሮ መንኮራኩሯን ፈልጎ ለማግኘት እንደቀደመው ዘመን በእርሳስና በወረቀት ቢሆን ከሚሊዮን አመት በላይ ይፈጅ ነበር። ከ1970 ጀምሮ የኮምፒውተር ቴክኖሎጂ እጅግ እየረቀቀ የሰው ዘርን በማስደነቅ ላይ ይገኛል።



ዛሬ ኮምፒውተር በቢሮ ብቻ ሳይሆን በሁሉ የስራ ዘርፍ ላይ ታላቅ ተጽዕኖ በማምጣት ላይ ይገኛል። ታዲያ ይህ የኮምፒውተር መራቀቅ የሰው ዘር ወደ ተሻለ ደስታና ምቾት አስገብቶታል? ወይስ የባሰ የእውቀት ብዛት ምድርን ወደ አለመርካትና ደስታ ቢስነት ከትቷታል? ባለንበት ዘመን እውቀት በሁሉ መስክ ጨምሯል፤ በተለይም በሰለጠኑት አገሮች እጅግ የሚያስገርም የትምህርትና የእውቀት ገበያ ተትረፍርፏል አሳዛኙ ነገር ግን እውቀት የሰውን ባህርይ ወደ እግዚአብሔር የበለጠ ሊያቀርበው ሲገባ እንደ ቀደመው አዳም ከእግዚአብሔር ርቆ በሁሉ አቅጣጫ ፍርስራሽ በዝቷል። ወጣቶች በእጽ ደንዝዘው፣ወንጀል በዝቶ፣ቤተሰብ ተበትኖ፣አመጽ ተንሰራፍቷል።





